የፋይናንስ ዘርፍ
የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

(የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የፋይናንስ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ
(የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስአበባ

የፋይናንስ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

(የሥልጠና ሞጁል)

አዘጋጅ፡ ዶ/ር ሀይለኢየሱስ ተሰማ (ጎንደር ዩኒቨርስቲ)

ዶ/ር ሻምበል ደምሌ (ጎንደር ዩኒቨርስቲ)

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኊላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ

© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ህዳር 2017 ዓ.ም

ማውጫ

መግቢያ....4
ምዕራፍ አንድ....9
የሙስና ወንጀል ምንነት....9
1.1 መግቢያ....9
1.2 የምዕራፉ ዓላማ....9
1.3 የተፈቀደው ሰዓት....10
1.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤(25 ደቂቃ)....10
1.5 የሙስና ምንነት....10
1.6 የሙስና ዓይነቶች....10
1.7 የሙስና ወንጀል ምንነት....11
1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች....15
1.9 በፋይናንስ ዘርፍ የሚከስቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች....23
ማጠቃለያ....30
ምዕራፍ ሁለት....32
የፋይናንስ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት....32
2.1 መግቢያ....32
2.2 የምዕራፉ ዓላማ....32
2.3 የተፈቀደው ሰዓት....32
2.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤....32
2.5 የፋይናንስ ሴክተሩን ለሙስና የሚያጋልጡ ምክንያቶች....33
2.5.1 ውስብስብነት....33
2.5.2 ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ....33
2.5.3 የቁጥጥር ተግዳሮቶች....34
2.2.5 ስልጣን እና ተፅዕኖ....36
ማጠቃለያ....39
ምዕራፍ ሶስት....40
በፋይናንስ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች....40
3.1 መግቢያ....40
3.2 የምዕራፉ አላማ....41
3.3 የተፈቀደው ሰዓት....41

3.4 የቡድን ውይይት ጥያቄዎች(41
3.5 ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት 42
3.5.1 የእምነት መሸርሸር (Erosion of Trust) 42
3.5.2 የኢኮኖሚ አለመረጋጋት (Economic Instability) 43
3.5.3 አለመመጣጠን (Inequality) 44
3.5.4 ልማትን ማዳከም (Undermining Development) 45
3.6 በፋይናንስ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት 47
3.6.1 የማነቃቂያ ጥያቄዎች(25 ደቂቃ) 47
3.6.2 በፋይናንሺያል ሴክተሩ ውስጥ ያሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን መታገያ ሰልቶች 47
3.6.2.1 የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት 48
3.6.2.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን 49
3.6.2.3 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ 50
3.6.2.4 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ 51
3.6.2.5 የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል 52
3.6.2.6 የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም /የስራ አካል ማድረግ 53
3.6.2.7 የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር 54
3.6.2.8 ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት 54
3.6.2.9 ክትትል እና ግምገማ 55
3.6.2.10 ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል 56
ማጣቀሻ 61
አባሪዎች 64

መግቢያ

አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ሙስና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በሆነበት የደህንነትና የፖለቲካ አንድምታ የሚያመጣ መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ እየወጡ ያሉ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ሃገራት ለእድገት የሚያደርጉትን ጉዞ በማሽመድመድ ዜጎች ለእንግልት ለሰላም ማጣትና ለስደት እንዲዳረጉ መንስኤ ሁኗል (World Bank, 2014)፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአገር አቀፍ እና በተለያዩ እርከኖች የሚገኙ መንግሥታዊና የልማት ተቋማት ልሙስና ተጋላጭነታቸው እየጨመረ ይገኛል (Transparency International, 2022)፡፡ በመሆኑም የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት አካታች፤ ሁልን አሳታፊና ብቃት ያላቸውን ተቋማት እንዳይገነቡ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ በዚህም የተነሳ ዘርፈ ብዙ መዘዞችን በማስከተል ላይ ይገኛል፡፡

የፌደራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለበርካታ ዓመታት በመንግስት የሚወጡ ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ በማስተዋወቅና ስልጠና በመስጠት ሙስናና ብልሹ አሠራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ተግባራት ውስጥም ጥናት እና ምርምር በማድረግ፣ አጀንዳ ቀርፆ ውይይት በማድረግ፣ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት በተጨማሪም ሚንስትሪምን በመጠቀም ስለ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ህብረተሰቡን በማንቃት ሙስናን ለመከላከል ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ በኮሚሽኑ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ግን ለሙስና ስጋት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ አደረጃጅቶችና አሰራሮችን በመለየት ወቅታዊ መፍትሄ የመስጠት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ፣ ሙስና በየጊዜው እየተከሰተ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ፣ ህጋዊ እና ተቋማዊ እንዲሁም ማህበራዊ ችግር እየሆነ ይገኛል፡፡

በተለያዩ ተቋማት ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ዓይነቶች ፣ የሕጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ ተቋማዊ ባህል፣ ደካማ የአሠራር ሥርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ-ምግባር ጉድለት፣ የሥራ አካባቢዎች አለመመቻቸት እና አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የጥቆማ አቀራረብ፣

አያያዝ እና አፈታት ግልፅነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ ደካማነት ፣ ወዘተ እንደ ተቋማዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህና የመሳሰለት ክስተቶች በተለያዩ ተቋማት ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ተጋላጭነት አደጋ በሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል።

ሙስና በአለም ላይ ባሉ ባደጉም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ልማት እና ማህበራዊ መረጋጋት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል። ሙስና በፋይናንስ አስተዳደር ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። በአሁኑ ጊዜ ባንኮች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት በህገ ወጦች ላይ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ይህን እርምጃ አይፈጽሙም። ብዙ ባንኮች ለሙሰኞች ገንዘባቸውን የሚያስቀምጡበት ቦታ መስጠታቸውን ቀጥለዋል። ይህ ክፍተት የፀረ-ገንዘብ ማሸሽ ደንቦች አጠቃላይ የላላ አፈፃፀም እና ተገቢውን ጥንቃቄ የማያደርጉ መሆኑን ያሳያል።

በ2015 በሀገራችን በተካሄደው የፋይናንስ ዘርፍ ተኮር የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት እንደገለፀው እ.ኤ.አ. በ2010 ከተገመገሙ 124 ስልጣኖች ውስጥ፣ ሁለት በመቶው ብቻ የፋይናንሺያል አክሽን ግብረ ሃይል (FATF) ምክሮችን ሙሉ በሙሉ ያሟሉ ናቸው። ጥናቱ እንደሚያሳው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በከፍተኛ አደጋ ሁኔታዎች ውስጥ ትርጉም ያለው የተሻሻለ ጥንቃቄን አልተገበሩም (FSA 2011).

የፋይናንስ አስተዳደር እጦት መዘዙ ከባድ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ደካማ የፋይናንስ አስተዳደር የጸጥታውን ሴክተር በሕዝብ እና በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ለሚደርሱ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ እንዳይሆን ያደርጋል። የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሙስና በየደረጃው ያሉ ሰራተኞችን ሞራል እና ውጤታማነታቸውን ይጎዳል። ህዝቡ በፋይናሻል ሴክተሩ ያለውን አመኔታ ያሳጣዋል፣ ይህም ትብብራቸውን ከህዝብ ማግኘት አዳጋች ያደርገዋል። በፀጥታ ሴክተሩ የህዝብ ሀብት አጠቃቀም ላይ ሙስና እና የፋይናንስ ብልሹነት አስተሳሰብ የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል። በሙስና እና በፋይናንስ አስተዳደር እጦት ምክንያት የህዝብ ሀብት ሲመዘበር እና ያለግበባብ ሲባክን የደህንነት ሪፖርት ስለማይቀርብ ህዝቡ ሀብቱ በአግባቡ ለታለመለት አላማ እየዋለ መሆኑን የማወቅ መብቱ ውስን ነው። ስለሆነም ጋዜጠኞች የህዝብን ሀብት ለታለመለት አላማ እንዲውል ገለልተኛ የሆነ ትንታኔ እና በቂ መረጃ መስጠት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም የመንግስት

ባለስልጣናት ለህዝብ ሃብት አስተዳደር ሀላፊነት በመውሰድ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ማጋለጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ስልጠናው ስለ ሙስና እጠቃላይ ፅንሰ-ሃሳብ ፣ሙስና በፋይናንስ ተቋማት የሚያስከትለው ጉዳት፣ በዘርፉ የሚከሰቱ የሙስና ዕይነቶችን መለየት እና ሙስናን የመታገያ ስልቶችን በማካተት ይህ የማሰልጠኛ ሞጁል ተዘጋጅቷል፡፡

የስልጠናው አስፈላጊነት

በዛሬው ውስብስብ የፋይናንሺያል ገጽታ በሙስና እና በመከላከያ እርምጃዎች ላይ ውጤታማ ስልጠና አስፈላጊነት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የሥልጠናው ተሳታፊዎች በፋይናንሺያል ሴክተር እና ተጠሪ ተቋማት ውስጥ የተንሰራፋውን የተለያዩ የሙስና ዓይነቶች አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተነደፈ ሲሆን እነዚህን ተግዳሮቶች በብቃት ለመፍታት የሚረዱ መሳሪያዎችን በማስታጠቅ ነው፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአጭር ጊዜ የሥልጠና ጊዜዎች ለረጅም ጊዜ የሥነ ምግባር ባህሪ እና ስኬት ወሳኝ መሠረት ሆነው እንደሚያገለግሉ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች ከስልጠናው ያገኙትን ክህሎት በአፋጣኝ፣ በገሃዱ ዓለም ተግዳሮቶች ላይ በማተኮር እውቀታቸውን በዕለት ተዕለት ሥራቸው ላይ በፍጥነት መተግበር እንዲችሉ ያደርጋል፡፡ ይህ ተግባራዊ አካሄድ ስልጠናው ቲዎሬቲካል ብቻ ሳይሆን ከተሳታፊዎች ሚና ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በሥልጠና ቆይታቸው ተሳታፊዎች በድርጅታቸው ላይ ያለውን አንድምታ በመመርመር የሙስና ዘርፈ ብዙ ባህርያትን በጥልቀት ይመረምራሉ፡፡ በተቋሞቻቸው ውስጥ የታማኝነት ባህልን እንዲያሳድጉ በማስቻል ስለ ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ተዛማጅ የህግ ማዕቀፎች እና የስነምግባር ደረጃዎች ጠንካራ ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡

የሞጁሉ አደረጃጀት

ይህ ሞጁል በሶስት ቀናት ውስጥ እዲጠናቀቅ ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ዋና አላማው ሰልጣኞች በስልጠና ቆይታቸው ስለ ሙስናና ብልሹአስራር በቂ እውቀትና ግንዛቤ ይፈጥራል ተብሎ

በጥንቃቄ የተደራጀ እና የተሰነደ ነው፡፡ ስለሆነም ሰልጣኞች በቆይታቸው በእያንዳንዱ ቀን ስለ ሙስናና ብልሹ አሰራር የመከላከያ ስልቶች ሁለንተናዊ ግንዛቤን በመፍጠር ቀድሞ የነበራቸውን እውቀትና ግንዛቤ የበለጠ ከፍ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

``

በስልጠናው የመጀመሪያ ቀን፡- ሰልጣኞች ሰለ ሙስና መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳቦችን ፣ ትርጓሜዎችን፣ አይነቶች እና መገለጫዎች እንዲሁም የፋይናንስ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እንዲረዱ እና እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ተሳታፊዎቹ የተለያዩ የትግበራ ዘዴወች በተናጥል እንዲሁም በቡደን በመስራት ሙስናን የመለየት አስፈላጊነትን በሚያጎሉ ውይይቶች ላይ ይሳተፋሉ ፡፡ በእለቱ በቀጣይ ቀናት ለሚሰጡ ስልጠናዎች መንደርደሪያ ሃሰብ እዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

በሁለተኛው ቀን፡- ሰልጣኞች በፋይናንስ ዘርፍ የሚከስቱ ሙስናና በልሹ አሰራሮች እና በዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን የሚያስከትሉትን ጉዳት በሚሉ ጉዳዮች በቂ ግንዛቤ እና እውቀት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በእያንዳዱ ጉዳዮች ላይ ሰልጣኞች የተለያዩ የተግበራ ዘዴዎችን ያከናውናሉ (የቡድን ውይይት፣ሀሳብ የማፍለቅ፣የአስረጅ ናሙና እና እራስን የመገምገምያ ተግባራት ያከናውናሉ)፡፡

በሶስተኛው ቀን፡- ሰልጣኞች በፋይናንስ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶች ላይ ሰፊ እውቀት እና ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ሙስናን በመዋጋት እረገድ አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ አለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን በማቅረብ ከእኛ አውድ ጋር መሄድ እና መትግበር የሚችሉትን አሰራሮች በመለየት እንዲተገብሩ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይካሄዳል፡፡ በመጨረሻም ስለ ስልጠናው አስፈላጊነት በሰልጣኞች ጠቅለል ያለ አስተያየት ተሰጥቶበት ስልጠናው ይጠናቀቃል ፡፡

የሞጁሉ አጠቃላይ እና ንዑስ ዓላማ

አጠቃላይ ዓላማ፡- የስልጠና ተሳታፊዎች በስልጠና ቆይታቸው በፋይናንሺያል ሴክተሩ ውስጥ ሊከሰቱ በሚችሉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል በሚያስችል ደረጃ እውቀት ፣ ክህሎት እንዲሁም የተሻለ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ እና እዲያዳብሩ ታስቦ የሚከናወን የስልጠና አይነት ሲሆን በዘርፉ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን እንዴት መከላከልና መቆጣጠር እንዳለባቸው ሰፊ ግንዛቤ ይፈጥራል ተብሎ የተዘጋጀ ሞጁል ነው፡፡

ንዑስ አላማዎች፡- ሰልጣኞች ከዚህ ስልጠና በኋላ፡

1. ስለ ሙስና ወንጀል ምንነት እዲለዩ እና በሀገራችን ባአዋጅ የፀደቁ የሙስና የወንጀል አይነቶችን ያበራራሉ ይዝረዝራሉ ፣
2. የፋይናንስ ዘርፍ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት በዝርዝርና በምክንያት ያስቀምጣሉ፣
3. በዘርፍ የሚከስቱ ሙስናና ብልሹ አስራሮችን በተመለከተ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያብራራሉ ፣ እንዴት እንደሚከሰቱ ሂደቱን ይተነትናሉ ፣
4. በፋይናንስ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን የሚያስከትሉትን ጉዳት ከዚህ በፊት በዘርፉ የተረጋገጡ የአስረጅ ናሙና እንደ ምሳሌ በማቅረብ በጥልቀት እንዲገመግሙት እና አንዲተነትኑት በማድረግ ያስከተለውን ጉዳት በጥልቀት እንዲረዱት ይደረጋል፣ እንዲሁም
5. በፋይናንስ ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ ስልቶች በግልፅ ይዘረዝራሉ፡፡ በተጨማሪም የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተቋሙ፤ ሙስና ቢከስት ወይም ቢኖር እንዴት ወንጀሉን ማጋለጥ እና መከላከል እንዳለባቸው ሰልጣኞች ጥልቅ ግንዛቤ እና እውቀት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

የሥልጠና ዘዴዎች፡-በዚህ የስልጠና ሞጁል የምንጠቀማቸው የስልጠና ዘዴዎች፡- የቡድን ውይይት (Group discussion) ፤የማነቃቂያ ጥያቄዎች (Brainstorming Sessions) ፤አስረጅ ናሙና (Case studies) ፤ እራስን የመገምገሚያ ቸክሊስት እና የማጠቃለያ ጥያቄዎች በስልጠናው ወቅት ይተገበራሉ፡፡

ተተኳሪ ተቋማት

ይህ የስልጠና ሞጁል የሚያካትታቸው ተተኳሪ ተቋማት፡-ገንዘብ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ የዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት፣ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን፣ ኢትዮ-ጂቡቲ ምድር ትራንስፖርት አ/ማ እና ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ናቸው ፡፡

ስልጠናው በአጠቃላይ የሚወስደው ጊዜ፡- 24፡00 ሰዓት

የስልጠና መሳሪያዎች፦ በዚህ ስልጠና ጥቅም ላይ የሚዉሉት የመርጃ መሳሪያዎች ማርከር፣ፍሊፐ ቻርት፣ፕሮጀክተር ፣ ማሰተወሻ ደብተር እና እሰክበሪቶ ወዘተ...ናቸዉ፡፡

ምዕራፍ አንድ

የሙስና ወንጀል ምንነት

1.1 መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀበል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምዕራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ነው፡፡

በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ያለው ሙስና የፋይናንስ ተቋማትን እና የገበያዎችን ታማኝነት የሚጥሱ ሥነ ምግባር የጎደላቸው እና ሕገወጥ ድርጊቶችን ያጠቃልላል፡፡ ይህም እንደ ጉቦ፣ ማጭበርበር፣ የውስጥ ለውስጥ ንግድ እና ገንዘብን ማሸሽ የመሳሰሉት ተግባራትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በፋይናንስ ዘርፍ የሚከስቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምዕራፍ በፋይናንስ ተቋማት ሊከሰቱ ስለሚችሉ የሙስና አይነቶች የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

1.2 የምዕራፉ ዓላማ

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
2. በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤
3. በፋይናንስ ዘርፍ ስለሚሰተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራር አይነቶችን ይለያሉ እዲሁም ይዘረዝራሉ ፡፡
4. በፋይናንስ ዘርፍ የሚከስቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ያብራራሉ ወይም ይተነትናሉ ፡፡

1.3 **የተፈቀደው ሰዓት**
ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4፤30 ሰዓት

1.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤(25 ደቂቃ)
ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ፤
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

1.5 **የሙስና ምንነት**

የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤(15 ደቂቃ)
ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር በሚገባ ካጤናችሁ እና ከተረዳችሁ በሗላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ፡፡ 1. ሙስና የሚለው ቃል ሲነሳ በአዕምሯችሁ ምን ይመጣባችኋል ?

ቁልፍ ሀሳቦች

ሙስና የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዝቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሕግ ትርጉም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የተባለ ተቋም "ሙስና" የሚለዉን ቃል ሲፈታዉ እንዲህ ይላል፡፡ corruption is Defined as "Misuse Of Entrusted Power For Private Gain." በዚህ ትርጉም መሰረት "ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል" ነዉ የሚል ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ በመገልገል ጉዳይን አላግባብ ማንተት ወይም አላግባብ ፈቃድ በመስጠትና በማጽደቅ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል በሙስና ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይገልጻል፡፡

1.6 **የሙስና ዓይነቶች**

የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤(15 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር በሚገባ ካጤናችሁ እና ከተረዳችሁ በሗላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ፡፡

1. የተለያየ የሙስና አይነት እንዳሉ ያውቃሉ ? ለመዘርዘር ሞክሩ

ቁልፍሀሳቦች

የሙስና ወንጀሎችን አይነት የበለጠ ለመረዳ በሁለት ተከፍለዉ ቀላል እና ከባድ ወይም (petty and grand) በሚል ለመረዳት መሞከር ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ቀላል ሙስና በታችኛዉ ሀላፊነት እርከን ወይም በዝቅተኛ መጠን የሚፈፀሙትን በሚመለከት ሲሆን ከባድ ደግሞ በከፍተኛ ስልጣን እርከን ወይም በብዙ መጠን የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከባድ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) የሚችል ነዉ፡፡

1.7 የሙስና ወንጀል ምንነት

የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤(25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር በሚገባ ካጤናችሁ እና ከተረዳችሁ በሗላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ፡፡

1. ከዚህ በፊት በነበራችሁ እውቀትና ግንዛቤ የሙስና ወንጀል ማለት ምንድን ነው? እንዴትስ ይገለፃል ?

ቁልፍሀሳቦች

የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፡-

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *“... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል...”* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፉያና ምዝበራ እንዱሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን

አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፊፈላል፡፡ በዚህ መሰረት እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡-

ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption) ፡- ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሉዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ በትልልቅ የመሰረተ-ልማት ፕሮጀክቶች (የመንገድ፣ የግድብ፣ የባቡር መስመር፣ የቴሌኮም ወዘተ ግንባታዎች)፣ከፍተኛ ገንዘብን የሚያንቀሳቅሱ (ገቢዎች፣ ጉምሩክ፣ ባንኮች ፣ ኢንሹራንስ ወዘተ) እንዲሁም ምስጢራዊ በሆኑ ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴ ባላቸው የደህንነት እና የመከላከያና ተመሳሳይ መስሪያ ቤቶች(ለምሳሌ የጦር መሳሪያ ግዢዎች)፡፡

ከፍተኛ ሙስና በዋነኛነት በጉቦ፣ በማጭበርበርና በዝርፊያ የሚገለጽ ሲሆን ለአብነት ያህል እነዚህ መገለጫዎች በሚከተሉት ተግባራት ይከሰታል፡-

- በአገር ደረጃ በሚከናወኑ የጦር መሳሪያዎች ላይ በሚፈጸም ህገወጥ ግዥ (እንደጦር አውሮፕላኖች፣ ታንኮች መርከብ እና ልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎች በመሳሰለት)፣
- ህገወጥ በሆኑ ጨረታዎች በሚፈጸሙ ከፍተኛ የግንባታ ውሎች ወይም ስምምነቶች /ከፍተኛ የኤላክትሪክ ሃይሌ ማመንጫ ግንባታዎች፣
- ከፍተኛ የመስኖ እና የመጠጥ ውሃ ግድብ ግንባታዎች፣የመንገድ ሥራዎች፣ በከባድ ፋብሪካዎች ግንባታዎች፣
- ልዩ ልዩ ለአገር ውስጥ ምርት አገልግሎት የሚውሉ እንደማዳበሪያ፣ ኬሚካሎች፣ መዳህኒቶች፣የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እና የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች በሞግዚት በሚፈጸሙ ህገወጥ ግዥዎች፣
- ከፍተኛ የቴሌኮሚኒኬሽን፣የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦቶች ላይ በሚፈጸም ህገወጥግዥዎች እና የመሳሰለትን ያካትታል፡፡

ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)፡- ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና

አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን፣ በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግልት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዱሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበሉውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡ ለአብነት ያህል እነዚህ መገለጫዎች በሚከተለት ተግባራት ውስጥ እንደሚከሰቱ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

- በመንግስትና በህዝብ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ጉቦ መቀበል፣
- ፍተሻ ጣቢያ ላይ ጉቦ በመቀበል ብሎም ህገወጥ ዕቃዎችን ማሳለፍ፣
- የግብር ምደባን በጉቦ እና በመደለያ በመስራት ያልተመጣጠነ የገቢ ግብር ምደባ ማካሄድ፣
- በልዩ ልዩ የቢሮ መሳሪያዎች እና በተሽከርካሪ ግዥ እና ጥገና ወቅት በሚደረግ ማጭበርበር (ሰነድችን በመሰረዝና በመደለዝ)፣
- በልዩ ልዩ የወጪ እና ገቢ ሰነዶች ላይ ማጭበርበር (ሰነዶችን በመሰረዝ፣ በመደለዝ እና በማጥፋት)፣
- በልዩ ልዩ የግንባታ ፤ ጥገና እና የአገልግሎት ጨረታዎች የማጭበርበር ተግባር በመፈፀም፣
- ህገወጥ የትምህርት እና የህክምና ማስረጃ በመስጠት ወይም በትምህርት ወይም በስልጠና የተገኘን ሙያ ህገወጥ በሆነ መንገድ (ህዝብን ሊጎዳ በሚችል መልኩ) በመጠቀም የሚፈጸም ነው፡፡

ሲስተሚክ ሙስና (state capture)፡- የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርአት ማዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል

የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፋያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሁነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዱሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፋያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡

1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች(120 ደቂቃ)

1.8.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.8.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ የጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.8.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.8.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳዩ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.8.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤
በጠቅላላዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በማድረግ በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.8.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ

የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ፦ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል።

1.8.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም ፦ የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

1.8.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦ አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል።

1.8.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ፦ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ

ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.10 *ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት* (*አንቀፅ* 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.11 *ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት* (*አንቀፅ* 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

1.1.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤
ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኂላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ

ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤ በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.16 *መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ* (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጅል ያስጠይቃል፡፡

1.1.17 *ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት* (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠይቅም፡፡

1.1.18 *ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት* (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

1.1.19 *ማቀባበል* (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

1.1.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

1.1.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

1.1.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ

ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

1.1.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፣መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ… በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

1.1.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

1.1.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ የህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

የማጠቃለያ ጥያቄዎች፤(30 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. “ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት” በዘርፉችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘውትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ።
3. “ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና የገንዘብ ወንጀልን” ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ።

1.9 በፋይናንስ ዘርፍ የሚከስቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

1.9.1 የማነቃቂያ ጥያቄዎች

የማነቃቂያ ጥያቄዎች (25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ከተወያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ።

1. በፋይናንሺያል ዘርፍ ሙስናን እንዴት ይገልፁታል?
2. በፋይናንሺያል ተቋማት ውስጥ ምን ምን ዓይነት የሙስና ዓይነቶች ሊኖሩ ይችላሉ?
3. ከዚህ በታች በቀረቡት ምስል ‘ሀ’ እና ‘ለ’ ምን ተረዳላችሁ?

ምስል ሀ

ምስል ለ

1.9.2 **በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ የተለመዱ የሙስና ዓይነቶች**

1.9.2.1 **ጉቦ** (Bribery)

የቡድን ውይይት (25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ ።

1. በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ጉቦን እንዴት ይገለፃል? ሊወስዳቸው የሚችላቸው የተለያዩ ቅርጾች ምንድ ናቸው?
2. ግለሰቦች እና ድርጅቶች በጉቦ እንዲሳተፉ የሚያነሳሳቸው ጉዳይ ምንድን ነው? እነዚህ ተነሳሽነቶች በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ በተለያዩ ሚናዎች እንዴት ይለያያሉ?

ቁልፍ ሀሳቦች

ጉቦ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ከሚከሰቱት የሙስና ዓይነቶች አንዱ ሲሆን በተለያዩ መንገዶች የሚንፀባረቅ የሥነ ምግባር አሠራሮችን እና የገበያ ታማኝነትን የሚጎዳ ነው (Loughman & Sibery, 2011; Owolabi, 2007) ።ይህ የሚሆነው የገንዘብ ተቋማቱ ለህዝብ ባለስልጣናት ፣ ተቆጣጣሪዎች ወይም ሌሎች ውሳኔ ሰጪዎች ጥሩ አያያዝን ለማስጠበቅ ፣ የተገዢነት መስፈርቶችን ለማለፍ ወይም በቁጥጥር ውሳኔዎች ላይተጽእኖ ለማድረግ ገንዘብ ወይም ስጦታ ሲሰጡ ነው ። ለምሳሌ፣ ባንኮች ከተፎካካሪዎቻቸው በበለጠ ፍጥነት ፈቃድ ወይም ፍቃድ

ለማግኘት በጉቦ ሊሳተፉ ይችላሉ፣ይህም ፍትሃዊ ውድድርን ያዛባል ። በተጨማሪም ፣በፋይናንሺያል ድርጅቶች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች የማክበር ጥሰቶችን እንዲያዩ ወይም የማጭበርበሪያ ተግባራትን እንዲያመቻቹ፣ብልሹ አሰራሮችን የበለጠ እንዲያዘወትሩ ሊያደርግ ይችላል ። እንዲህ ዓይነቱ ጉቦ በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ከመሸርሸር ባለፈ የቁጥጥር ማዕቀፎችን ውጤታማነት ስለሚጎዳ ሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ ወደ መደበኛው ባህል ይመራል ።

1.9.2.2 ምዝበራ (Embezzlement)

ሀሳብ የማፍለቅ ተግባር (25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ከተወያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ፡፡

1. ከፋይናንሺያል ሴክተሩ አንፃር ምዝበራን እንዴት እንገልፃለን? ከሌሎች የማጭበርበር ዓይነቶች የሚለየው በምንድን ነው?
2. ከዝርፊያ በስተጀርባ ያሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድ ናቸው?
3. በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ምዝበራ መከሰቱን የሚጠቁሙ አንዳንድ የተለመዱ ምልክቶች ወይም አመላካች መንገዶች ምንድ ናቸው?

ቁልፍ ሀሳቦች

ምዝበራ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ የተንሰራፋ የሙስና አይነት ሲሆን ይህም ለግለሰብ ወይም ለድርጅት ለግል ጥቅም በአደራ የተሰጠውን ገንዘብ አላግባብ መጠቀምን ያካትታል፡፡ ይህ በተለምዶ የሚከሰተው ሰራተኞች ወይም ስራ አስፈፃሚዎች ለራሳቸው ጥቅም ከኩባንያው ሂሳቦች ገንዘብ ሲቀይሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሰራተኛ ገንዘብን ለማጥፋት የውሸት ደረሰኞችን ሊፈጥር ወይም የሂሳብ መግለጫዎችን ሊቀይር ይችላል፣ ይህም ለተቋሙ ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ ያስከትላል፡፡

ምዝበራ የድርጅቶችን የፋይናንስ መረጋጋት አደጋ ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን የባለሀብቶችን እምነት የሚጎዳ እና በአጠቃላይ የፋይናንሺያል ሴክተሩን ስም የሚያበላሽ ተግባር ነው፡፡ ውጤቶቹ

በኢኮኖሚው ውስጥ ሊሽከረከሩ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት የሥራ ኪሳራ እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይቀንሳል።

1.9.2.3 ገንዘብ ማጭበርበር (Money laundering)

የቡድን ውይይት(25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ።

1. ሕገወጥ ገንዘብ ምንድን ነው? ከሌሎች የገንዘብ ወንጀሎች የሚለየው እንዴት ነው?
2. ገንዘብ ማጭበርበር በምን አይነት መንገድ ሊከናወን ይችላል?

ቁልፍሀሳቦች

የገንዘብ ማጭበርበር ገንዘቡ ህጋዊ መስሎ እንዲታይ ለማድረግ በህገ ወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ አመጣጥ በተለይም ውስብስብ የፋይናንስ ግብይቶችን ወይም ህጋዊ አካላትን በሚያካትቱ ዝውውሮች የመደበቅ ሂደት ነው። ወንጀለኞች የገንዘብ ማጭበርበርን በመጠቀም የመጀመሪያውን ህገወጥ የገንዘብ ምንጭ በመደበቅ እና ከህጋዊው ኢኮኖሚ ጋር በማዋሃድ ገንዘቡን ያለምንም ጥርጣሬ እንዲጠቀሙ ወይም ኢንቨስት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ጉልህ የሆነ የሙስና አይነት ነው (Arewa, 2019; Lyman, 1999; Villányi, 2021)። የገንዘብ ማጭበርበር በተለምዶ በሦስት ደረጃዎች ይከፈላል(Schneider, 2000)፡-

ምደባ፡- ሕገወጥ ገንዘቦች በመጀመሪያ ወደ ፋይናንሺያል ሥርዓት ይገባሉ። ይህ ገንዘቡን በባንኮች ውስጥ ማስቀመጥ፣ ንብረቶችን መግዛት (ለምሳሌ፣ ሪል እስቴት ወይም የቅንጦት ዕቃዎች) ወይም ገንዘቡን በካዚኖዎች ወይም ጥሬ ገንዘብ በሚሳተፍባቸው ሌሎች ንግዶች ማስተላለፍን ሊያካትት ይችላል። ግቡ ገንዘቡን ከወንጀለኞች እጅ እና ወደ ፋይናንሺያል ስርዓት ማዛወር ነው።

ንብርብር፡- ይህ ደረጃ የገንዘቡን ምንጭ እና ባለቤትነት ለማድበስበስ የተነደፉ ውስብስብ የፋይናንስ ግብይቶችን ያካትታል። በሂሳቦች መካከል ብዙ ዝውውሮችን፣ ምንዛሬዎችን መለወጥ ወይም ውስብስብ በሆኑ የፋይናንስ መሳሪያዎች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስን ሊያካትት ይችላል። ዓላማው የገንዘቡን አመጣጥ በተቻለ መጠን አስቸጋሪ ለማድረግ ነው።

ውህደት፡- በዚህ ደረጃ፣ የተጭበርበረው ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው ይመለሳል፣ በተለይም በህጋዊ ኢንቨስትመንቶች ወይም ግብይቶች። ገንዘቡ እንደ ህጋዊ ገቢ ወይም ኢንቨስትመንቶች በመምሰል ጥርጣሬን ሳያሳድግ አሁን ጥቅም ላይ ይውላል።

1.9.2.4 **የውስጥ ለውስጥ ንግድ** (Insider trading)

ሀሳብ የማፍለቅ ተግባር (25 **ደቂቃ**)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ከተወያቻሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ።

1. ከውስጥ አዋቂ ንግድ በስተጀርባ ያለው ተነሳሽነት ምንድን ነው? ግለሰቦች እና ድርጅቶች እንዴት ይጠቀማሉ?
2. የውስጥ ንግድ የፋይናንሺያል ገበያዎችን ታማኝነት እና ፍትሃዊነት እንዴት ይነካል?

ቁልፍሀሳቦች

የውስጥ ለውስጥ ንግድ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ የተለመደ የሙስና አይነት ሲሆን ይህም ስለ አንድ ኩባንያ ይፋዊ ባልሆኑ ቁሳዊ መረጃዎች ላይ ተመስርተው ዋስትናዎችን መግዛት ወይም መሸጥን ያካትታል። ይህ ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር የሚከሰተው እንደ ሥራ አስፈፃሚዎች፣ ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሚስጥራዊነት ያለው መረጃ የማግኘት መብት ያላቸው ግለሰቦች እውቀታቸውን ተጠቅመው በገበያ ላይ ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም ሲያገኙ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ የኩባንያው የውስጥ አዋቂ ስለ መጪው ውህደት ወይም በይፋ ከመገለጹ በፊት ከፍተኛ የገቢ መቀነስ ካወቀ፣ በመረጃው ላይ ተመስርተው አክሲዮኖችን በመገበያየት መረጃ በሌላቸው ባለሀብቶች ወጪ ትርፍ ሊያገኙ ይችላሉ።

የውስጥ ለውስጥ ንግድ የባለሀብቶችን እምነት ስለሚሸረሽር እና የዋስትናዎችን ትክክለኛ ግምት ስለሚያዛባ ለፋይናንሺያል ገበያዎች ታማኝነት አስፈላጊ የሆኑትን የፍትሃዊነት እና ግልጽነት መርሆዎችን ያበላሻል።

1.9.2.5 ሰነድ ማጭበርበር (Fraud)

የቡድን ውይይት (25 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ ፡፡

1. ሰነድ ማጭበርበርን በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ እንዴት እንገልፃለን? በተለምዶ የሚያጋጥሟችሁ የሰነድ ማጭበርበር ዓይነቶች ምንድ ናቸው?
2. ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ሰነድ ማጭበርበር እንዲፈጽሙ የሚገፋፋቸው ጉዳይ ምንድን ነው? ኢኮኖሚያዊ፣ግላዊ እና ድርጅታዊ ሁኔታዎች እንዴት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ?

ቁልፍሀሳቦች

ማጭበርበር በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ የተንሰራፋ የሙስና አይነት ሲሆን ይህም ህገ-ወጥ ጥቅምን ለማስጠበቅ ያለመ ሰፊ የማታለል ድርጊቶችን ያጠቃልላል(Alexander & Cumming, 2022 ;Rafay,2023)። ይህ የዋስትና ማጭበርበር እና የሂሳብ መግለጫዎችን ማጭበርበርን ጨምሮ ብዙ ቅጾችን ሊወስድ ይችላል፡፡

የዋስትና ማጭበርበር፡- ይህ ከዋስትና ግዢ ወይም ሽያጭ ጋር በተያያዘ የተለያዩ የማታለል ድርጊቶችን ያጠቃልላል፡፡ የተለመዱ ምሳሌዎች የውስጥ ለውስጥ ንግድ፣ የኩባንያውን የፋይናንስ ሁኔታ የተሳሳተ መረጃ መስጠት እና የአክሲዮን ዋጋን ለመቆጣጠር የውሸት መረጃ ማሰራጨትን ያካትታሉ፡፡

የሂሳብ መግለጫ ማጭበርበር፡- ይህ ሆን ተብሎ የሂሳብ መግለጫዎችን በተሳሳተ መንገድ ማቅረብን ያካትታል ስለ አንድ ኩባንያ የፋይናንስ ጤና የተሳሳተ አመለካከት ለመፍጠር፡፡ ይህ ገቢን ከመጠን በላይ መግለጽ፣ እዳዎችን ማቃለል ወይም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ለማታለል የተነደፉ ማጭበርበሮችን ሊያካትት ይችላል፡፡

አስረጅ ናሙና 1፡ ACB የሙስና ውንጀላ።(40 ደቂቃ)

ዳራ

ACB ባንክ በሙስና ወንጀል በተለይም የውጭ ምንዛሪ ክምችት መመዝበር እና የተንሰራፋውን የመልካም አስተዳደር እጦት በተመለከተ ከፍተኛ ክስ ቀርቦበታል። ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ያሉ ስርአታዊ ጉዳዮችን ለመረዳት ወሳኝ ሲሆን ሙስና በኢኮኖሚ መረጋጋት እና በህዝብ አመኔታ ላይ ያለውን ተጽእኖ አጉልቶ ያሳያል።

ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ክምችት በ ACB ውስጥ ባሉ ባለስልጣናት አላግባብ መመዝበሩን ሪፖርቶች ገልፀዋል። የምርመራ ጋዜጠኞች በፋይናንሺያል መዝገቦች እና ግብይቶች ላይ ልዩነቶችን አግኝተዋል። ህዝባዊ ተቃውሞዎችን እና የተጠያቂነት ጥያቄዎችን አስነስቷል። ይህም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አስተዳደር እና ዓለም አቀፍ የውጭ ኢንቨስትመንትን የመሳብ አቅም ላይ ስጋት ፈጥሯል።

የቡድን ውይይት ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ ።

1. ከቀረበው የጉዳይ ጥናት ምን አይነት የሙስና ተግባር ተፈፅሟል ብለው ያምናሉ?
2. በ ACB ውስጥ ለሙስና አስተዋጽኦ ያደረጉ ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድ ናቸው?
3. በፋይናንሺያል ተቋማት ውስጥ ያለው ሙስና ህዝቡ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት በምን መንገድ ይነካል?

አስረጅ ናሙና 2፡ በፋይናንሺያል ዘርፍ የፍላጎት ግጭቶችን ማስተዳደር (40 ደቂቃ)

ዳራ

በታዋቂው የፋይናንስ ተቋም XYZ ባንክ ውሰጥ በርካታ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ከባንኩ የህዝብ ግዴታዎች ይልቅ ለግል ለቤተሰቦቻቸው፣ እዲሁም ለጓድኞቻቸው ፋይናንሺያል ጥቅም ቅድሚያ እንደሚሰጡ መረጃ ያሳያሉ ። እነዚህ ሥራ አስፈፃሚዎች ለቤተሰባቸው አባላት ወይም ለቅርብ አጋሮቻቸው በቀጥታ የሚጠቅሙት ብድሮችን እና ኢንቨስትመንቶችን በማጽደቅ ላይ ተሳትፈዋል፣ ይህም የጥቅም ግጭቶችን ፈጥሯል። ይህ ሁኔታ ለባንኩ የገንዘብ ኪሳራ እና የህዝብ አመኔታ አሳጥቷል። በXYZ ባንክ ውስጥ ያሉ ከፍተኛ የስራ አስፈፃሚዎች የቤተሰብ አባላት እና የንግድ

ባለቤቶች የሆኑ የቅርብ ጓደኞች ነበሯቸው። እነዚህ ሥራ አስፈፃሚዎቹ ለእነዚህ ከላይ ለተጠቀሱትን ግለሸቦች ተገቢውን ፋይናንስ ህገና ደንብን መሰረት ሳያደርጉ ግልጽነት በጎደለው አሰራር ብድር አጽድቀው ለቤተሰቦቻቸው እና ለቅረብ ጓደኞቻቸው እዲጠቀሙ አድርገዋል ።

የውይይት ጥያቄዎች

1. በXYZ ባንክ ውስጥ ያሉ የስራ አስፈፃሚዎች ምን አይነት የስነምገባረ ጥሰት ፈጽመዋል?
2. በ XYZ ባንክ ውስጥ ግልጽ የሆነ የስራ ባህል አለመኖሩ ለሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረገው በምን መንገድ ነው? የጥቅም ግጭቶችን ለመቆጣጠር የተቋሙ የስራ ባህል ምን ሚና ይጫወታል?
3. ኦዲተሮች በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ያሉ የጥቅም ግጭቶችን ለመቆጣጠር ምን ሚና ይጫወታሉ? እንደ XYZ ባንክ ያሉ ተቋማትን የስነ ምግባር ባህሪን ለማሳደግ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ ይችላሉ?
4. የጥቅም ግጭቶችን በተመለከተ ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ከ XYZ ባንክ ጉዳይ ምን ትምህርት ሊማሩ ይችላሉ? እነዚህ ትምህርቶች የራሳቸውን አሠራር ለማሻሻል እንዴት ሊተገበሩ ይችላሉ?

የጋራ ውይይት ነጸብራቅ (20-25 ደቂቃዎች)

ከዚህ ክፍል ምን ተምረዋል? በቡድን በመሆን ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች መሰረት የዚህን ምዕራፍ ሀሳቦች አጠናክሩ።

1. በፋይናንሺያል ግብይቶች ወይም ግንኙነቶች ውስጥ የጉቦ ሁለት ምሳሌዎችን ያቅርቡ? በጉቦ ውስጥ መሳተፍ ሊያስከትሉ የሚችሉ ህጋዊ እና የስነ ምግባር ውጤቶች ምንድ ናቸው?
2. ምዝበራ እንዴት ይገለጻል? እና ከሌሎች የስርቆት ዓይነቶች እንዴት ይለያል? ግለሰቦች ምዝበራ እንዲፈጽሙ አንዳንድ የተለመዱ ግፊቶች ምንድ ናቸው?
3. ገንዘብ ማጭበርበር ምንድን ነው? በሂደቱ ውስጥ የተካተቱት የተለመዱ ደረጃዎች ምንድናቸው? ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ለምን በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ውስጥ ይሳተፋሉ? የ"ህገወጥ" ገንዘብ ምንጮች ምንድናቸው?

ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል። በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል። ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው። የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይ እና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል።

በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ያለው ሙስና በተለያዩ ጎጂ ልማዶች የሚገለጥ ስራ እና መሰሪ ተግባራት ማለትም ጉቦ፣ ገንዘብ ማጭበርበር፣ ገንዘብ ማሸሽ፣ የውስጥ ለውስጥ ንግድ እና ማጭበርበር የሚያካትት ሲሆን ጉቦ፣ የተለመደ ዘዴ፣ የስርዓቱን ታማኝነት የሚያዳክም በፋይናንሺያል ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ ክፍያዎችን መስጠት ወይም መቀበልን ያካትታል። ምዝበራ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ የተንሰራፋ የሙስና አይነት ሲሆን ይህም ግለሰቦች የአደራቦታቸውን አላግባብ በመጠቀም ገንዘባቸውን ለግል ጥቅማቸው ሲጠቀሙ ነው። ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ የተራቀቀ እቅድ፣ በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ህጋዊ ለማስመሰል ምንጩን መደበቅን ያካትታል። የውስጥ ንግድ፣ ፍትሃዊ የገበያ አሰራርን መጣስ፣ ልዩ መረጃ ያላቸው ግለሰቦች እውቀታቸውን ለገንዘብ ጥቅም ሲጠቀሙበት ነው። ማጭበርበር፣ የተለያዩ የማታለል ድርጊቶችን የሚያካትት ፣ የውሸት ሪፖርት ማቅረብን፣ የተሳሳተ መረጃ መስጠትን እና ህዝቡ በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት የሚሸረሽሩ ሌሎች ታማኝ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሊያካትት ይችላል። እነዚህ መሰሪ ተግባራት በግለሰብ ባለሀብቶች ላይ ጉዳት ከማድረስ ባለፈ አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ያናጋሉ፣ እድገትና ልማትን ያደናቅፋሉ።

ምዕራፍ ሁለት

የፋይናንስ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት

2.1 መግቢያ

የፋይናንሺያል ሴክተሩ የማንኛውም ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደመሆኑ የኢኮኖሚ እድገትና ልማትን በማሳለጥ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይሁን እንጂ ይህ ዘርፍ እንደማንኛውም ተቋም ለሙስና የተጋለጠ ነው፤ ይህም በግለሰብም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ አስከፊ መዘዝ ያስከትላል። ይህ ምዕራፍ ለፋይናንስ ሴክተሩ ለሙስና ተጋላጭነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን፣ ላይ ያተኩራል።

2.2 የምዕራፉ ዓላማ

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የፋይናንስ ዘርፍ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት ያብራራሉ ፤
2. በሀገራችን የፋይናንስ ሴክተሩን ለሙስና የሚያጋልጡ ዋናዋና ምክንያቶች ይዘረዝራሉ፤

2.3 የተፈቀደው ሰዓት

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:30 ሰዓት

2.4 የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር በሚገባ ካጤናችሁ እና ከተረዳችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አብራሩ።

1. የፋይናንስ ሴክተሩን በተለይ ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. በፋይናንስ ዘርፍ የሚስተዋለው ሙስና በኢኮኖሚው ላይ ሰፊ አንድምታ አለው ብለው ያምናሉ? ከሆነ እንዴት?

2.5 የፋይናንስ ሴክተሩን ለሙስና የሚያጋልጡ ምክንያቶች

2.5.1 ውስብስብነት (Complexity)

ሀሳብ የማፍለቅ ተግባር (15 ደቂቃ)
ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡ 1. በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ውስብስብነትን እንዴት ይገልጹታል? ቁልፍ ባህሪውስ ምንድን ነው? 2. የፋይናንስ ምርቶች ውስብስብነት ለተጠቃሚዎችም ሆነ ለተቆጣጣሪዎች ውሳኔ መስጠትን የሚያደናቅፍ በምን መንገድ ነው? ይህ ሁኔታ ወደ ሙስና ሊያመራ የሚችልበትን መንገድ ያብራሩ?

ቁልፍ ሀሳቦች

የፋይናንሺያል ግብይቶች ብዙ ጊዜ የተወሳሰቡ ኔትወርኮችን እና ውስብስብ ሂደቶችን ያካተቱ ሲሆን ይህም ህገወጥ ድርጊቶችን ለመቆጣጠር እና ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ውስብስብነት የፍይናንሻል ሂደቶችን በማደብዘዝ እና ተጠያቂነትን በመሸርሸር ለሙስና ከፍተኛ ተጋላጭነትን ይፈጥራል፡፡ በፋይናንሺያል ቴክኖሎጂ አስተዳደር ውስጥ ያሉ ውስብስብ ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ለመረዳት አዳጋች ናቸው፣ ይህም ብልሹ አሰራርን በቀላሉ እንዳይታወቅ ያደርገዋል፡፡ የቢሮክራሲያዊ መሰናክሎች ግለሰቦቹ ለግል ጥቅማቸው ወደ ሚጠቀሙባቸው ምቹ መንገዶች ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ስርአቶች ውስብስብ ባህሪ ሃላፊነትን በማስፋፋት ስነ-ምግባር የጎደለው ባህሪ ከቁጥጥር ለማምለጥ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ውስብስብ ባህሪ የሙስና ወንጀል በሚፈጸምበት ወቅት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን ከሕዝብ እይታ ተደብቀው እዲቆዩ ስለሚያደርግ በተቋማት ላይ የግልጽኝነት ችግር ይፍጥራል፡፡

2.5.2 ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ (Large Amounts of Money)

የቡድን ውይይት (15 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ ።

1. ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ለሙስና ምቹ ሁኔታን እንዴት ይፈጥራል?

ቁልፍ ሀሳቦች

ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በተለያዩ ተያያዥ ምክንያቶች የተነሳ ለሙስና ተጋላጭ ይሆናል። ምክንያቱም ከፍተኛ የገንዘብ ምንጮች በሚሳተፉበት ጊዜ ለግል ጥቅም ያለው እምቅ በግለሰቦች እና በድርጅቶች መካከል ሥነ ምግባራዊ ያልሆነ ባህሪን ሊያበረታታ ይችላል።

በፋይናንሺያል ተቋማት ውስጥ የሚፈሰው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለሙስና፣ ለማጭበርበር እና ለሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ ብዙ እድሎችን ይፈጥራል። ባለሙያዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በሚሳተፍበት ጊዜ ለግል ጥቅማቸው ለማዋል ያለው አቅም ይጨምራል። ገንዘቦችን ለማግኘት ከሥነ ምግባር ውጭ የድርጅቱን የፋይናንስ ስርዓት ለጥቅማቸው እንዲጠቀሙበት ቀላል ያደርገዋል።

በፋይናንሺያል ተቋማት ውስጥ የሚፈሰው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ለሙስና፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ ጉቦ፣ የውስጥ ንግድ እና ማጭበርበር በርካታ እድሎችን ይፈጥራል። በተጨማሪም የፋይናንሺያል ግብይቶች መጠነ ሰፊ ተጠያቂነትን ሊያደበዝዝ ስለሚችል የገንዘብ ፍሰትን ለማወቅ እና ህገወጥ ተግባራትን ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል። የፋይናንስ ሥርዓቶች ግልጽ ባልሆኑባቸው አካባቢዎች፣ ግለሰቦች አሻሚዎችን ለግል ጥቅማቸው ሊጠቀሙበት ይችላሉ፣ ይህም እምነትን የበለጠ ይሸረሽራል። ከዚህም በላይ የፋይናንስ ግቦችን ለማሳካት የሚደረገው ጫና ወደ ሥነ ምግባር ብልሹነት ሊያመራ ስለሚችል ብልሹ አሠራሮች መደበኛ እንዲሆኑ ያደርጋል።

2.5.3 የቁጥጥር ተግዳሮቶች (Regulatory Challenges)

የቡድንውይይት (15 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አቅርቡ ።

1. አሁን ባለው የቁጥጥር ማዕቀፎች ውስጥ ሙስና በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ እንዲስፋፋ የሚፈቅዱ ዋና ዋና ክፍተቶች ምንድ ናቸው?
2. ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ነባር ደንቦች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው? የእርስዎን አመለካከት የሚደግፈው ምን ማስረጃ ያቀርባሉ?

ቁልፍ ሀሳቦች

የቁጥጥር ተግዳሮቶች የቁጥጥር እና የማስፈጸሚያ ዘዴዎችን በማወሳሰብ ለሙስና ከፍተኛ ተጋላጭነቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ። የቁጥጥር ተግዳሮቶች በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ሙስናን በማጎልበት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። ደካማ፣ ወጥነት የሌለው የፋይናንስ ደንቦችን ማስከበር ሙሰኛ ተዋናዮች ክፍተቶችን የሚጠቀሙበት፣ ከምርመራ የሚሸሹበት እና እንደ ገንዘብ ማጭበርበር፣ ጉቦ እና ሌሎች ህገወጥ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉበትን አካባቢ ይፈጥራል።

ውስብስብ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ደንቦች ለባለሥልጣናት የፋይናንስ ግብይቶችን ለመቆጣጠር እና ለመከታተል አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። ይህም ስለ ስርዓቱ የተራቀቀ እውቀት ላላቸው ሰዎች ለግል ጥቅም ደንቦችን እንዲቆጣጠሩ እድል ይሰጣቸዋል። ይህም ብልሹ አሰራሮች ቁጥጥር ሳይደረግባቸው እንዲያብቡ ያስችላቸዋል። ከዚህም በላይ የቁጥጥር ሂደቶች ግልጽነት ማጣት አድልዎ እና ጉቦ የተለመዱበትን አካባቢ ሊያዳብር ይችላል። ምክንያቱም ባለድርሻ አካላት በውጤታቸው ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ይፈልጋሉ።

2.5.4 ግልጽነት ማጣት (Lack of Transparency)

ሀሳብ የማፍለቅ ተግባር (15 **ደቂቃ**)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለተሳታፊዎች አቅርቡ።

1. በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ግልጽነትን እንዴት ይገልጹታል?

2. ግልጽነት ማጣት በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ለሚፈጸሙ ብልሹ አሰራሮች ዕድሎችን የሚፈጥር በምን መንገድ ነው? ምሳሌዎችን መስጠት ይችላሉ?

ቁልፍሀሳቦች

በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ግልጽነት ማጣት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን በማደብዘዝ እና ሥነ ምግባር የጎደለው ባህሪ ቁጥጥር ሳይደረግበት እንዲሄድ በማድረግ ለሙስና ከፍተኛ ተጋላጭነት ሆኖ ያገለግላል። መረጃ በቀላሉ በማይገኝበት ወይም በማይደረስበት ጊዜ ባለድርሻ አካላት ድርጊቶችን በብቃት መመርመር አይችሉም ። ይህም ብልሹ አሰራሮች ሊዳብሩ የሚችሉበትን አካባቢ ይፈጥራል። ይህ ግልጽነት ብዙውን ጊዜ ወደ መረጃ አለመመጣጠን ይመራል፣ በስልጣን ላይ ያሉት ደግሞ መረጃን ወይም ውሳኔዎችን ለጥቅማቸው ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤ ይህም ፍትሃዊነትን እና ተጠያቂነትን ይጎዳል ።

ለሪፖርት ማቅረቢያ እና ቁጥጥር ግልፅ ዘዴዎች ከሌሉ ግለሰቦች እንዳይታወቁ ሳይፈሩ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት እንዲፈጽሙ ስለሚበረታቱ ጉቦ፣ አድልዎ እና ማጭበርበር የመፍጠር እድሉ ይጨምራል ። በተጨማሪም ከግልጽነት እጦት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የህዝብ አመኔታ መሸርሸር የሙስና ተግባራትን የበለጠ ሊያጎለብት ይችላል። በመጨረሻም ግልጽነት አለመኖሩ ሙስናን ከማመቻቸት ባለፈ የአስተዳደርን ታማኝነት እና በህዝባዊ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ያዳክማል።

2.2.5 ስልጣን እና ተፅዕኖ (Power and Influence)

የቡድን ውይይት (15 ደቂቃ)

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድናችሁ መሰረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለሌሎች ቡድን ተሳታፊዎች አስረዱ ።

1. በፋይናንሺያል ሴክተሩ ውስጥ ስልጣን እና ተፅዕኖ ለሙስና ከፍተኛ ተጋላጭነትን ይፈጥራል ብለው ያምናሉ? ከሆነ በምን መንገድ?

2. በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ሥልጣንና ተፅዕኖ ቁጥጥር እና ክትትል ካልተደረገበት የሚያስከትለው ጉዳት ዘርዝሩ?

ቁልፍ ሀሳቦች

በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ያለው ስልጣንና ተፅዕኖ ለሙስና ከፍተኛ ተጋላጭነትን ይፈጥራል። ጥቂቶች በገንዘብ ነክ ውሳኔዎች ላይ ትልቅ ስልጣን ሲይዙ፣ አቋማቸውን ለማስጠበቅ ወይም ለማሻሻል እንደ ጉቦ ወይም ሽርክና የመሳሰሉ ስነ-ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶች ሊፈጽሙ ይችላሉ። ይህ የኃይል ማጎሪያ ተጠያቂነት እጦት ሊያስከትል ይችላል፤ምክንያቱም ተደማጭነት ያላቸው ተዋናዮች ከምርመራ ሊያመልጡ ይችላሉ ወይም ደረጃቸውን በመጠቀም የቁጥጥር ሂደቱን ያዳክማሉ። በተጨማሪም የፋይናንሺያል ገበያው ውስብስብ ባህሪ ብዙውን ጊዜ የገንዘብ ፍሰትን ያደበዝዛል፤ለተቆጣጣሪዎች እና ህዝቡ ግብይቶችን በብቃት ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ፈታኝ ያደርገዋል።

የኃይል ተለዋዋጭነት መስተጋብር የፍላጎት ግጭቶች እየተበራከቱ የሚሄዱበት አካባቢን ሊያበረታታ ይችላል። ይህም የሥነ ምግባር ደረጃዎችን የበለጠ ይሸረሽራል። ዞሮ ዞሮ በፋይናንሺያል ሴክተር ውስጥ ሥልጣንና ተፅዕኖ ቁጥጥር ካልተደረገበት፣ የገበያ ታማኝነትን የሚያበላሹና ሕዝቡ በፋይናንስ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት የሚሸረሽሩ ብልሹ አሰራሮችን ሊያመቻቹ ይችላሉ።

አስረጅ ናሙና 1፡በአንድ የከተማ የህዝብ ገንዘብ ምዝበራ፡፡(55 ደቂቃ)

ዳራ

